MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Department of Facilities Management
DIVISION OF SUSTAINABILITY AND COMPLIANCE

አባሪ- A

# MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
# AVAILABILITY OF ASBESTOS MANAGEMENT PLAN
**2021-2022**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
የአስቤስቶስ ማኔጅመንት እቅድ መኖሩን ስለመግለጽ

ኦክቶበር 1986፣ የዩ.ኤስ. ኮንግረስ ስለ አስቤስቶስ አደገኛነት የወሰደው የፈጣን እርምጃ ምላሽ ህግ - "Asbestos Hazard Emergency Response Act (AHERA)" በዚህ ህግ መሠረት፣ በህዝብ እና የግል የኤለመንተሪ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስቤስቶስ ችግሮችን ለመፍታት አጠቃላይ መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል። እነዚህ ደምቦችና መመሪያዎች አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች በቀላሉ የሚፈረካከስ እና የማይፈረካከስ አስቤስቶስን እንዲፈትሹ/እንዲቆጣጠሩ፣ በትምህርት ቤት ህንፃዎች ላይ የአስቤስቶስ አደገኛነትን የማሻሻል ማኔጅመንት እቅድ እንዲያዘጋጁ፣ እና ወቅታዊነትን የጠበቀ የምላሽ እርምጃ መውሰድ  እንደሚያስፈልግ ይደነግጋሉ።

እነዚህ ደምቦች-መመሪያዎች ለትምህርት ቤቶች በርካታ ሃላፊነቶችን ይሰጣሉ። እነዚህን ኃላፊነቶች ስለማከናወን የእኛ አስቤስቶስ ማኔጅመንት ፕላን ከዚህ በታች ተዘርዝሯል። ይህ እቅድ የተመደበውን ሰው፣ አርኪቴክት፣ ወይም የኢንጅነር ደብዳቤ፣ ስለማሳወቅ ሒደት፣ ማረጋገጫዎች፣ እና ቀን የተጻፈበት ዓመታዊ የማሳወቂያ ቅጅዎችን ማካተት አለበት።

ለአዳዲስ ህንፃዎች፣ ከኦክቶበር **12/1988** በኋላ የተጠናቀቁ፣ የእኛ "የማኔጅመንት እቅድ-**management plan**" ይህንን ማሳወቂያ እና የማስወገጃ ዶኩሜንቶችንም ይጨምራል። ይህ ማስረጃ፦ በእኛ ግንዛቤ፣ ምንም አይነት አስቤስቶስ ያለው የህንፃ መሥሪያ ማቴሪያሎች ጥቅም ላይ አለመዋሉን ወይም በዚህ ህንጻ ላይ ለመጠቀም የተገለጸ ነገር የለበትም ማለት ነው።

ይህንን እቅድ ያለምንም ወጪ ወይም ገደብ ሳይኖር በመደበኛ የሥራ ሠዓቶች መመልከት ይቻላል።

ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎ በዚህ አድራሻ ይከታተሉ፦ Mr. John Conaway, environmental health specialist, Environmental Services/Indoor Air Quality Unit, Division of Maintenance, at 240-740-2331 or John_D_Conaway@mcpsmd.org.